# <u>ቦካሳ</u>

በቦካሳ ርእስ የተዘጋጀች ይህች ጦማር፤ ርዕሰ ደብር አብርሃም “በመንበረ ዕልወት ዘነግሰ ለአዝማናት፦ ጣዖተ ሕሊና ቦካሳ አኮኑ ሰአርኪ”ብለው በቫቲካን ጋርዶች አምሳል ያደራጁቸውን ወጣቶች በከንቱ ውዳሴ እያጋጋሉ ከወገኖቻቸው ጋራ ለማጋጨት ካቀረቡት ቅኔ የተወለደች ናት።

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ
nigatuasteraye@gmail.com የካቲት አስር / ፳፻፰ ዓ.ም

ሊያጠቃህ የፈለገ ሲፎክርብህ “ወደፈተና አታግባን ” የምትለዋን ጸሎት ፈጥነህ አስብ እንጅ መመከቻ ወይም የምትደበድብበት ብትር ለመፈለግ አትፍጠን። “ወደፈተና አታግባን” ካልክ ለጠላትህም ማሰብህን የሚመለከት አምላክ የጠላትህን በትር በእጅህ ይጥልለሀል። በእጅህ በወደቀው በጠላትህ በትር ጠላትህን ብትጎዳው “ድንጋይን በሰው ላይ ቢያዳኗት፡ ተመልሳ ባናት” እንደሚባለው ዳዊትም ”ወትወርድ አመጻሁ ዲበ ድማሁ” እንዳለው ፤ በራሱ እጅ ራሱን እንደደበደበ ስለሚቆጠር በሰማይም በምድርም ነጻ ነህ“ ብለው ኢትዮጵዮጵያውን አባቶች አስተምረውናል።

ፈታኝና አስቸጋሪ ነገር ሲገጥመኝ ለመግለጽ የምሞክረው በቤተ ክርስቲያናችን ሕጽን የነበሩ ሊቃውንት አበው ኢትዮጵያ ባቋረጠችባቸው ዘመናት ያጋጠሟትን መከራና ደስታ በገለጹባቸው በቅኔወቻቸውና በስሜታቸው ነው። ስህተት መሆኑን ህሊናየ ከነገረኝ፤ እውነት አለመሆኑን እያወኩ የዘመኑ ሰው ስለማይወደው ይጠላኛል፤ ይሸሽኛል፤ ይርቀኛል፤ ይዘልፈኛል ብየ ከመናገር እንደበቴን አልገታም። ከንቱ ውዳሴና ክብር ለማግኘት፤ የከንቱ ውዳሴና ክብር ትርፍ ምንጭ ከሆኑት ዘመናውያንና ብዙ ቍጥር ከሚያጅባቸው ጋራ በመሰለፍ ከማገኘው ክብር፤ ሽልማትም ሆነ ሹመት ምንጫቸውን ሞት ካደረቀባቸው፤ ሊረዱኝና ሊደግፉኝ ሞት ከከለከላቸው በህይወት ከሌሉ ሰዎች ጋራ መሰለፉን እመርጣለሁ። ሰማይ ዝቅ መሬት ከፍ ቢል ሊቃውንት ለማይቀበሉት ቤተ ክርስቲያንን አገርንና ወገንን ለሚጎዳ ነገር ህሊናየን መቃብር ማድረግ ፈጽሞ አልፈልግም። እስካሁን ያዘጋጀኋቸውን ምንባባት ያቀርባኳቸው ሁሉ በዚህ መንፈስ “ወደፈተና አታግባን” እያልኩ ነው። አባቶች እንዳሉትም በጻፍኳቸው ጦማሮች ሁሉ እውነትን ለመግለጽ ርእስ ፍለጋ ደቂቃ አጥፍቼ አላውቅም። በእውነት ላይ የተወረወረችውን ድንጋይ ገልብጨ ሳያት ብዙ ጫጭቶች የታቀፈች ዶሮ ሆና አገኛታለሁ። <u>ለዚህች ጦማር ርዕስ</u> ለመሆን የበቃቸው <u>ቦካሳ የምትለው ቃልም በዚህ መንገድ</u> በእውነት ላይ ከተወረወረችው ተጸንሳ ያገኘኋ እንጅ ፈልጌ ያመጣኋት አይደለችም። የኔ ሀላፊነት በምጥ ላይ ያገኘኋትን ለማዋለድ ብእር መፈለግ ነው። ይህች ቦካሳ የተባለች ጦማር ተጸንሳ የተገኘችበት፤ ርዕሰ ደብር አብርሃም ቅኔ ብለው የወረወሩት የስድብ ድንጋይ ከዚህ በታች እነሆ !

“በመንበረ ዕልወት ዘነግሰ ለአዝማናት፦ ጣዖተ ሕሊና <u>ቦካሳ</u> አኮኑ ሰአርኪ”

የቅኔው ትርጉም፦በክህደት መንበር ላይ ለዘመናት ነግሶ የኖረው <u>ቦካሳ</u> የተባለው ከሹመቱ መሻሩን ነው የሚያሳየው።

ቦካሳ የተባለው ንጉሥ ማነው? የካደውስ ምንድነው? መቼ ነው የካደው?ብየ ባካባቢው ያሉትን ሰዎች አነጋገርኩ። እሱም "ደፍተሮች ተሰብስበው አንተንና ሊቀ ማእምራን አማረን ያወዙበት ጉዳይ ነው" ነው አሉኝ። ደፍተሮች ያወዙበት ነገር ምንድነው? ብየ ጠየኩ። እሱማ "ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ካንድ እስከ ሁለት ጊዜ እያከታተሉ በፊርማቸው አቡነ ማትያስን እየዘለፉ ደብዳቤ የጻፉበት ነው" አሉኝ። የሰማ ህዝብ ምን ታዘበ? ብየ ጠየኩ።

"ብዙው ህዝብ ምን ጥቅም አገኝበታለሁ? የቀረው ጫጫታው በደመቀበት፤ የመንግሥት ደጋፊው ሰብረው ከገቡት ጋራ፤ እናቶች በጣም ተምታቶባቸዋል? ቄሶች ደግሞ የሚፈልጉት ገንዘብ ሲሆን የፖለቲካውን ግለትና ነፋስ እየተመለከቱ ህይወታቸውን የሚገፉ ናቸው እንጅ ስለነገረ መለኮት መዛባት ስለ ሞራል ስለ ሀገር መናጋት ስለ ህዝብ ጭንቀት የሚሰማቸው አይደሉም" አሉኝ።

እኔም ቀጠልኩና "ደፍተሮች አወገዝንበት የሚሉት ነገርም ቢሆን፤ የሃይማኖቱ የበላይ ጠባቂ ነኝ ከሚሉት ከሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ደብር አንድ ሰው አምጥቶ ከንሳስ ኪዳነ ምህረት ላይ ነሰነሰው። በአቡነ ይስሀቅ አማካይነት ወደ መጣበት ወደ ሊቀ ሊቃውንት መለስኩት፤ ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህና አቡነ ማትያስ ተጻጻፉበት፤ እኔም ባለብኝ ሀላፊነት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የሚሰጣትን ግንዛቤና አክብሮት በማያሻማ መንገድ የተማርኩትን በካህናት ማሰልጠኛም ሳስተምረው የነበረውን ለሚመለከተው ሁሉ አቅርቤአለሁ። መረዳት ከፈለጉ ይህን ስንሰለት ይጫኑ "ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም በሮማ ካቶሊክ በፕሮቴስታንትና በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትያላት ግንዛቤና አክብሮት"

ያቀረብኩት ምስክርነት ማንም ሊክደው ሊጨምርበትና ሊቀንስለት የሚችለው አይደለም። ከዚያ የወጣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተከታይ እንዳልሆነ ተናግሬአለሁ። ይህ ደግሞ የኔ የግሌ አይደለም። የኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋህዶ ግላዊ አቋምም አይደለም። ኦርቶዶክስ ከሚያደርጓት መሰረታውያን ትምህርቶችና ከቀሩት ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ጋራም አንድ ከሚደርጓት አንዱ ነው። አገሬን ለቅቄ እስከወጣ ድረስ የነበረ። የተማርኩትና ሳስተምረው፤ በዝማሬና በቅዳሴ የነበረ ነው። እንዲያውም ኦርቶዶክሳዊ መሰረተ እምነት የለወጠ ያናጋ ካለ በታሪክ፤ በመላ ኦርቶዶክስና በእግዚአብሄር ይጠየቃል" አልኳቸው። ቀጠልኩና "ከዚያ አልፎ በዚህ ጉዳይ ይወገዝ ከተባለ መጀመሪያ መወገዝ ያለባቸው ሊቀ ማእምራን አማረ ሳይሆኑ ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ናቸው። ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህን በመሪነት እየተጠቀሙ ለምን ሊቀ ማእምራን አማራን ብቻ ለይተው ያወግዛሉ? አልኳቸው። እሳቸውም መለሱና "ተመልካች ሰውማ ቢኖር፤ ደፍተሮቹ የከሰሱበትን የነገሩን ጭብጥ ለቀው ለዳኛው ሊቀ ማእምራን ማርያምን ስለካዷት ሻርናቸው አይሉም ነበር" አሉኝ። እኔም ነገሩ ገረመኝና "ሸፍጡ ሀሰቱ ማስመሰሉ ክህደቱ ገንዘብ መውደዱ ጥላቸው አንድ ላይ እየተለወሰ የከተማውን ህዝብ ሁሉ አቡካክቶታል አይሉኝም? ስላቸው በሳቅ ሊፈነዱ።

ለምን ሳቁ? ስላቸው፤ "የቅኔ ነጠቃዎ ስልት ስለገረመኝ ነው። በተጨማሪም "ደፍተሮቹ ግብር እንደተጠራ የክት ልብሳቸውን እየለበሱ ጥምጥማቸውን እየከሸኑ መቋሚያቸውን እያዘመሙ፤ አጼ ቴወድሮስ በጠሩት አደባባይ ላይ ተሰብስበው መጡ። አጼ ቴወድሮስም በነጭ ጥምጥምና ልብስ በረዶ መስሎ የፈሰሰውን ምድረ ደፍተራ ሲመለከቱ። ያቺ ቆማጣ ቆመጥማጣ ራሷን ጠምጥሚ ወገቧን ሰባቂ ሁላ አስቸገረችኝ አይደል? (የታንንት ምሥጢር ገጽ 89) ያሏቸውን ደፍተሮች የሚመስሉ ዛሬ በዲሲ ሸንጎ አደባባይ ብቅ አሉ። ካሉኝ በኋላ "የደፍተሮችን ነገር እንተዎውና በዚህ ርእስ የሚሉትን ይበሉና እንማርበት" ብለውኝ ተለያየን። እንዳሉት እንማርበት። ቦካሳ! ቦካሳ! ቦካሳ ! ይገርማል እጅግ ከመጠን በላይ ቦካሳ ! እያልን የቦካውንና እንዴት እንደቦካ እንመልከተው።

ቦካሳ ባእድ ቃል ነው። በዚህ ስም ሲጠሩ የነበሩት ሰው ኢትዮጵያዊ አይደሉም። ለምን ቦካሳ እንደተባሉ የሚያውቁት የሰውየው ወላጆቹ ናቸው። ለነሱ እንተወዎና ቦካሳ የሚለውን በራሳችን ሰዋሰዋዊ ስልት እንመልከተው። ስለ ቋንቋ የምታጠኑ እነ ዲበአቶ መስፍን አረጋን እንድታርሙኝ እየጠየኩ ይህችን ቃል ባለችኝ ትንሽ አቅሜ ስመለከታት፤ ኢትዮጵያ አገራችን፤ ህዝባችንና ቤተ ክርስቲያናችን ያሉበትን ጠቅላላ ሁኔታ የምትገልጽ ቃል ሆና ነው የተረዳኋት።

ለመግለጽ እሞክራለሁ። ቦካን ሳ ከምትባለው ፊደል መለየት አለብን። ሳ ሁለት ስሜት ታሳያለች። የሚያስገርም የሚያስደነግጥ ነገር ለሚነገር ግስ አጎላማሽ አጠያያቂ ስሜት አላት። የ ሳ ን አገባብ እንመልከት።

## ቦካ ሳ

ነገሮች የሚረከሱት ያለቦታቸው ሲውሉ እንጅ ርኩስ የሚባል ነገር የለም። የርክሰት ምንጭ ጌታችን "እኩይ ብእሲ እም እኩይ መዝገቡ ልቡ ያወጽአ ለእኪት፤ ወሠናይ ብእሲ እምሠናይ መዝገበ ልቡ ያወጽአ ለሠናይት" (ማቴ 12፡ 35) ። እንዳለው የህሊና መቆሸሽ ነው። ለምሳሌ፡- ኮቴን በምጠቀምበት መንገድ ሱሪየን ልጠቀም ብል፤ ጫማየን በምጠቀምበት መንገድ ኮፍያየን ብጠቀም ያለቦታቸው ስለ አዋልኳቸው አረከስኳቸው ማለት ነው። ኮቴንና ኮፍያየን ያለ አገባብ እንድጠቀም ያደረገኝ የህሊናየ መዛባት እንጅ ችግሩ ከኮቱ ወይም ከኮፍያው አይደለም ማለት ነው።

መጀመሪያ "በሥምረትከ ምላዕ ውስተ አልባቢነ . . . . እንተ ታለብስ ሞተ" (ሥ ቅ ገ 85) "ሞት ከምታደርስ ከቂም ከተንኮል ሕሊናችንን አጽዳልን" እያልን በምንቀድሰው ቅዳሴ መሰረት ህሊናችን የኃጢአት መጠንሰሻ ወይም ማቡኪያ እቃ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን። በሀሰት በጥላቻ በሸር ህሊናችን ከረከሰ፤ ካፋችን የሚፈልቀው የምንናገረው የምናስበው ነገር ሁሉ በኃጢአት የቦካ ይሆናል።

የአማረኛ ግሥ ሳ የምትለውን ፊደል ተንተርሳ ብቅ ካለች የነገሩን ጽንሰ ሀሳብ ወደ አነጋጋሪነት የመለወለጥ ኃይል አላት። ለምሳሌ የተለወሰ ዱቄት ወይም አፈርና ጭድ ተቀላቅሎ ተለውሶ ሲቆይ በሚፈጠሩት ተውሳኮች ከተጠበቀው በላይ ተለጥጦ ቀድሞ ከነበረው ሰፍቶ ና ተነፍቶ ሲታይ በመገረም ቦካሳ ይባላል። ግለ ሰብም ሆነ ድርጅት ወይም መንግስት የሚፈጽመው በደልና ኃጢአት ተጠራቅሞ ከመጠን ሲያልፍ ቦካሳ ይባላል።

ርዕሰ ደብር አብርሃም ቦካሳ እያሉ የተናገሯትን ቃል፤ ባንድ ወቅት መምሕሬ ነበሩ እያሉ የጠቀሷቸው የየኔታ ጌራ ጓደኛ የተናገሩት ትንግርት በራሳቸው በርዕሰ ደብር አብርሃም የተፈጸመ መሰለኝ። ለትምህርት ወደ ፈረንጅ አገር ስለሚላኩ ተማሪዎች ተነስቶ በተካሄው ጉባኤ ላይ "የራሳችንን ትምህርት ሳናስተምር ወደ ፈረንጅ አገር የምልካቸው ልጆቻችን ፤ ባዶ ሸክላ እንደመላክ ነው። የሚማሩት በማያውቁት ቋንቋ ስለሆነ ይከብዳቸውና ከተላኩበት ትምህርት ቤት ቁም ነገር መቅሰም ሲያቅታቸው፤ ከትምህርት ቤት ውጭ የሚያዩትን አተላ ዝቀው እያመጡ የሚደፉብንን መጥረግ ያቅተናል" ብለው ነበር። ዛሬ ርዕሰ ደብር አብርሃም ከነበሩበት አየር ላንድ ከተማ ዝቀው አምጥተው እየደፉብን ያለው አተላ፤ ከመጠን በላይ ቦክቶ ወጣቱን ሁሉ ስላጥለቀለቀው በቀላሉ ተዝቆ የሚያልቅ አይደለም።

"ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት" በሚል ጠልሰም አቡክተው በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሚለጥፉት ጭቃ ተማርኳቸው ያሏቸውንና የተማሩባቸውን ቦታዎች እንድንፈትሻቸው ያደርገናል። በቅድስት ሀገር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ አየርላንድ በሚገኘው Holy ghost missionary collage Diblin እና በለንደን ፍልስፍና ሳኮሎጂ ነገረ መለኮትና ኢኮኖምክስ ተምሬ ዲግሪ ተቀብያለሁ ብለዋል። እነዚህ ተማርኳቸው የሚሏቸው የትምህርት አይነቶች በራሳቸው ንግግር ሲመዘኑ አቦኳቸው እንጅ ሊማሯቸው ቀርቶ በጥጋቸው አልደረሱም። የርእሰ ደብርን አቡኪነት ለመረዳት በጠልሰሟቸው ያቦኳቸውን ከዚህ በታች እጠቅሳለሁ።

1ኛ አኅት አብያተ ክርስቲያናትን ሳታማክር የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በ1854 ያወጀችው በሃይማኖት ሳይሆን በፖለቲካ ባህርዩዋ ወሰነች እያሉ ገጽ በጠለሰሙት (ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት ገጽ 91)

2ኛ፡፡ ካቶሊኮቹ አመቺ የመሰላቸውን ጊዜ ጠብቀው አዲስ ህገ ሃይማኖት እንዲወጣላቸው እንደሚጠይቁ ( ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት ገጽ 107)

3ኛ" ካቶሊኮች ማንንም ሳያዋያዩ በተናጠል ማርያማዊ ነገረ እምነትን በዶግማ ደረጃ አከታትለው ማወጃቸውን ኦርቶዶክሶች ይቃወማሉ (ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት 177)

4ኛ። ነገር ግን ከ1854 ወዲህ አብዛኞቹ ኦርቶዶክሶች በተለየዩ ምክንያቶች አይቀበሉትም (ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት ገጽ 89)

5ኛ "የኢትዮጵ ቤተ ክርስቲያንና የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በእመቤታችን እንደሚስማሙ እንመለከታለን"ይልና (ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት 85)። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መስመር አልፋ በካቶሊክ መንገድ አትሄድም። ሆኖም በቃላት ተመሳሳይነት የተነሳ በአምልኮ ማርያም መታማቷ አልቀረም" (ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት 107)

6ኛ ካቶሊካውያን አባቶች ለቤተ ክርስቲያን መከፋፈል ምክንያት ከሆነው ከኬልቄዶን ጉባዔ (ጉባዔ ከልባት) በፊት የነበሩ ስለሆኑ ትምህርታቸውን ባግባቡ መቀበል ተገቢ ነው" (ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት 151)

7ኛ ቤተ ክርስቲያናችን በቁርባን አማናዊነትና በሌሎችም ህግጋተ ሃይማኖት የምትስማማ መሆኗ እየታወቀ እመቤታችንን ጥንተ አብሶ አላገኛትም ካለች ካቶሊክ ሆነች ማለት ሚዛናዊ ያልሆነ ክስ ነው" (ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት ገጽ 85)

8ኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በ451 የተካሄደውን ጉባዔ ከለባት ባለመቀበሏ አሁን በነገረ ማርያም ከእነሱ (ከኦርቶዶክሶች) ብትለይ የሚያስፈራት ወይም የሚቀነስባት ምን ሊኖር ይችላል?(ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት 195)

9ኛ ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የበለጠ የእመቤታችንን ቅድስና የገለጸ እንደሌለ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የለም። ርዕሰ ደብር "ከሰው ትርፍ ለማግኘት ስትል ወይን አለቀባቸው አለች" ብሎ ማቅረቡ (ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት ገጽ 188 )

"አስቀድሜ ማረጋገጥ የምፈልገው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን የሃይማኖት አባቶች ብለን የምንቀበላቸ በጻፉትና በተናገሩት ፍጹማን ናቸው ብለን አይደለም" (ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት ገጽ 187)

10ኛ ስህተት አለባቸው የሚላቸውን የኦርቶዶክሳውያን መጻህፍት እየተጠቀመ እምነታቸውን እየነቀፈ የላቲንን እንቀበል እያለ፤ እንደገና መጽሀፋቸውን እየተጠቀሙ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ መቅደስ ለመቀደስ መድፈራቸው።

በዚህ መሳይ ንግግራቸው ኦርቶዶክስንና ሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን እርስ በርስ ከማደበደብ አልፈው በሁለቱም ላይ እየዘመቱ ናቸው። የኦርቶዶክሱንና የየሮማ ካቶሊክን ግንዛቤ ለይተው ባለማወቃቸው ሁለቱንም በጨቀየው ህሊናቸው አንድ ላይ በማቡካታቸው በሁለቱም መወገዝ የሚገባቸው ናቸው። "ኢታክብር ዕቡየ ወኢትስሀል ሎቱ መጻሕፍተ አላ ላእሌሁ ግብር ሎቱ ወኢትኩን ናፋቄ እንዘ ትጼሊ ወሐሊ ዘተመነይከ ወይፈጽም ለከ አምላክከ" (125፡ 14) የሚለው ኦርቶዶክሳዊው መመሪያችን፤ ቦካሳ እያሉ በመያውቁት ገብተው የሚያቦኩትን መስተዋድያን፤ ባቦኩበት ጠልሰም ጠቅልለውና ገንዘው ኦርቶዶክሶችና ካቶሊኮች ከቤተ ክርስቲያን ቅጽር ከማራቅ በቀር የሚጠቅሱላቸው መጽሐፍ የለም። በርእሰ ደብር ጠልሰም ምክንያት በዚህች ጦማር የተጠቀሳችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ፡-

1ኛ፡-የሮማ ካቶሊክ እምነት ተከታዮች ኢትዮጵያውያን ወገኖች

2ኛ፡-በስዊስ ጋርድ አምሳል ተደራጅታችሁ በግብረ ኃይልነት የተሰለፋችሁ ወጣቶች

3ኛ፡-ርዕሰ ደብር አብርሃም ባቦኩት ንክኪ ይህች ጦማር የጠቀሳቻችሁ ምናልባት ቅር የሚያሰኛችሁ ቃል ብታገኙ ፤ ያነሳሁበት ምክንያት F 8 20016 በዋሽንግተን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በተከናወነው ግብዣ እጅግ ቦክቶ

የቀረበውን ለማጽዳት እንጅ፤ እኔ እንደ ርእሰ ደብር አብርሃም ከምንም ተነስቼ በጥላቻ ወይም በጥቅም ተገፍቼ ያደረኩት አለመሆኔን፤ ከዚህ በታች በማቀርባቸው ማሳሰቢያ አማክይነት ከይቅርታ ጋራ እንድትረዱልኝ በትህትና እጠይቃችኋለሁ።

## 1ኛ የሮማ ካቶሊክ እምነት ተከታዮች ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ

የኦርቶዶክሱን ነገረ መለኮት በቃል ያስተማሩ ጽፈውም ያወረሱ ከነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፤ ቅዱስ ቄርሎስ፤ ቅዱስ ባስልዮስ፤ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ፤ መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ እስከ እና የኔታ ብርሃኑና የኔታ ቢረሳው ድረስ የነበሩ ሊቃውንት፤ የላቲንን ቅዳሴና መዝሙር ወደኛ፤ የኦርቶዶክሱን ነገረ መለኮትና ስርአተ አምልኮ ወደ እናንተ ቤተ ክርስቲያን በመክተት የሚቀላቅሉትን እንድንቃወም አስተምረውኛል።

ጣሊያኖች የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን በመጠቀም ርእሰ ደብር አብርሃምን የመሳሰሉ ሰዎች የፈጸሙት ታሪካዊ ጠባሳ እንዳለ ሆኖ፤ በውስጧ ስላሉ የዋህን ቅዱሳን ክርስቲያኖች ለቤተ ክርስቲያኗ ክብር አለኝ። ሆኖም እኔ ቀርቶ አስተዋይ የሆነ ሁሉ ርእሰ ደብር አብርሃም "ማርያማዊ ህገ ሃይማኖት" በሚል ጠልሰም እጅግ በኰመጠጠ ቡካት ያቦኩትን ክብርና ድጋፍ የሚሰጥ ይኖራል ብየ አልገምትም።

የኢትዮጵያዊት ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን መምህራን "በሌላ ሰው መሰረት ላይ እንዳልሰራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ስፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርኩ" (ሮሜ 15:20) እያለና "እያንዳንዱ እግዚአብሔር እንደ ጠራው ይመላለስ" (1ኛ ቆሮ 7:17) እያለ ቅዱስ ጳውሎስ ደጋግሞ ያስተማረውን ሐዋርያዊ ትውፊት እንዳስተማሩን፤ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ይህን የቅዱስ ጳውሎስን ትእዛዝና መመሪያ እንደምትቀበለው አምናለሁ።

የቅዱስ ጳውሎስን ሐዋርያዊ ትውፊት ከተቀበልን፤ እንደነዚህ የመሳሰሉትን አቡኪዎች በጋራ ልንቃወማቸው ሐዋርያው ትውፊት ያዝዘናል። በዚህ ትውፊት መሰረት የፕሮቴስታንታዊነትም ይሁን የካቶሊካዊነት ያተረጓጎም መንገድና ስርአተ አምልኮ ወደኛ ሰርጎ መግባቱን እኛ ኦርቶዶክሳውያን እንደማንፈቅድ፤ የኛ የኦርቶዶክሱ እምነትም በፕሮቴስታንትና በሮማ ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሰርጎ እንዲገባ አንደግፍም። ነገር ግን በዚህ ዘመን በገጠመን ፈተና ሳይማሩ ፤ እንደ ቤታችን አነጋገር ምሥጢር ሳያደላድሉ ወይም በውጩ አነጋገር በcomparative theology ሳይበስሉ፤ ገንዘብ ባለበት ሁሉ ሰርገው የገቡ እንደ ርዕሰ ደብር የመሳሰሉ አቡኪዎች በሚፈጥሩብን ችግር ምክንያት፤ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በመቤታችን ላያ ያላትን አመለካከት ደጋግሜ ጠቅሻለሁ።

የጠቀስኩበትም ምክንያት ታሪክ የሚያስተምረንን ለመግለጽ እንጅ፤ እነ ርዕሰ ደብር አብርሃም ይዘው የመጡብንን በዘመኑ የነበሩት የሮማ ቤተ ክርስቲያን ፓፓ በ1854 ለምን በራሳቸው ቤተ ክርስቲያን አውጀው ከተቱ ብየ ለመንቀፍ አይደለም። ቢቻላችሁና ፈቃዳችሁ ቢሆን እውነት ነውና፤ እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች ይህ የኛ ነው ከኦርቶዶክስ አትቀላቅሉብን ልክ አይደላችሁም ብላችሁ ልትገስጿቸው ክርስቲያናዊ ባህርይ የሚጠይቃችሁ ይመስለኛል።

## 2ኛ:-በቫቲካን ጋርዶች አምሳል ርዕሰ ደብር አብርሃም ያደራጀቻችሁ ወጣቶች

በርእሰ ደብር አብርሃም ተሰይማችሁ በተሳሳተ ቅኔ ከንቱ ውዳሴ በመታለል ላይ ያላችሁና፤ በሌላው ወገናችሁ በመወቀስ ላይ ያላችሁ ወጣቶች ወገኖቻችን፤ በዚህች ጦማር የጠቀስኳችሁ፤ ርዕሰ ደብር ቤተ ክርስቲያናችን

በማትቀበለው መንገድ ለግል ጥቅማቸው ይሁን ለፖለቲካ ተባባሪዎችና ምኞታቸውን አስፈጻሚዎች አርገው ስለቀረቧችሁ ብቻ ነው።

በመላ ኢትዮጵያውያን ዘንድ እንደሚታወቀው፤ መንግሥትን ለመቃወም በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ሁሉ እኛን አስመስሎ ሽረኞችን እያሰለጠነ በማደራጀት ተለጣፊ በሚል ስም በመሀላችን እያስገባ ያፈርሰናል እያሉ በመንግስት ላይ ሰፊ ወቀሳና ክስ አለ። በሀገርና በወገን የሚደረገውን ስህተት እየገለጸ የሚቃወም ግብረ ኃይል በዋሽንግተን ዲሲ ዙሪያ እንዳለ የታወቀ ነው። ይህ ግብረ ኃይል በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከሰተውን ነገር ለመታዘብ ሞክሯል። በግብራቸው በመጽሀፋቸው እምነቱን የካዱ ሰዎች ህዝቡን በጠሉት ላይ ቀስቅሰው ለማስጠላትና በጎናቸው ለማሰለፍ በተመሳሳይ ስም እናንተን ተለጣፊ አድርገው እንዳደራጁችሁ በሰፊው እየተነገረ ነው።

ታዲያ እናንተን በዚህ ስም አደራጅቶ ያሳለፋችሁ አካል የመንግስትን ተግባር በቤተ ክርስቲያን ፈጸመ። እናንተ ተለጣፊወች ናችሁ ብሎ ተመልካች ቢወቅሳችሁ ልክ ነው ከማለት በቀር ማስተባበል ትችላላችሁ? ነገሮችን በስድብ፤ በዘለፋና በኃይል ከግብ ለማድረስ ከመሞከር ይልቅ ገለል በማለት የገባችሁበትን በጥሞና ብትመለከቱት ዘግይቶ ከሚደርስባችሁ ጸጸት የምትድኑ ይመስለኛል። ሁሉም ያልፋል ጥሎት የሚልፈው ጠባሳ ግን ለዘላለም ይኖራል።

በአጽንኦ ላሳሰባችሁ የምሞክረው፤ አሁንም ሆነ ወደፊት የምትነቀፉበት እስካሁ በሰራችሁት አይደለም። "በቀና መንገድ ምሩን ልንሳሳት እንችላለን" እያላችሁ የተናገራችሁትን ዓለም አይቶታል። ይህ ተገቢ ጥያቄያችሁ ገርነታችሁንና ባላወቃችሁት ነገር መልካም መስሏችሁ እንደ ገባችሁበት ሁሉም ተረድቶላችኋል። በዚህም ቪድዮውን ከገጻችሁና ከድምጻችሁ ጋራ ቀርጾ ለዓለም ያቀረባችሁን ግለ ሰብ ልታመሰግኑት ይገባል። በቅኔ እያወደሰ በመደለል ያቦካውን ነገር ሁሉ ለመፈጸም መሳሪያ ያደረጋችሁን ግለ ሰብ ግን ልትወቅሱት ይገባችኋል። "ልንሳሳት እንችላለንና ምሩን " ከሚለው ድምጻችሁ ጋራ በቪዲዮ የቀረጻችሁ ሰው ግን ከታሪካዊ ፍርድ ነጻ አውጥቷችኋልና አክብሩት ውደዱት።

የጎዳችሁት ወገን ካለ "ልንስሳት እንችላለን" በምትለው ቃላችሁ ገርነታችሁን ተረድቶ ይቅር ሊላችሁ ይገባዋል። እስካሁን በተጓዛችሁበት የፈጸማችሁት ኃጢአት ካለ የፈጠራችሁ አምላክ እንደሰው ጨካኝ አይደለም ይቅር ይላችኋል። የምትወቀሱት፤ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "ወዘሰ አክበርዎ በንባብ ወወድቀ በፈቃዱ ወኮነ ከመ እንስሳ ዘአልቦ ልብ ይትኴነን ጥቀ በሕሊናሁ" (ሃይ 68፡29) እንዳለው፦እውነቱ በቃል በጽሑፍ በማስረጃ እየየተነገራችሁ የምትቀጥሉበት ሲሆን ብቻ ነው። ምሩን የምትሏቸው ሰዎች በሮማ ካቶሊኮች ካድሪናል ስርአት እንጅ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ስርአትና እምነት አለመሆኑ ራሳቸው እየነገሯችሁ ስለሆነ በቀላሉ መረዳት ትችላላችሁ።

እስካሁን የሰጧችሁን አመራር ታዘቡ፤ ካሁን ጀምራችሁ ርቃችሁ ከመሄዳችሁ በፊት አስቡ። ይህን ስል ለቤተ ክርስቲያንና ለራሳችሁም አደገኛነቱን ለማሳየት እንጅ ከነ ርእሰ ደብር አብርሃም ጋራ ያላችሁን ወገናዊ አንድነትና ፍቅር ለማገደፍረስና ለማሻከር አይደለም። "ሲወለድ ያጠለቀውን ጥብቆ ሲሞት አወለቀው" እንዲሉ እነርዕሰ ደብር አብርሃም ከልጅነታቸው ጀምሮ ሲሰሩት የነበረውን የኃጢአት ከል፤ እናንተን እያለበሷሁ ነውና አስቡበት። እነሱ ያጋጋሉትን የወጣትነት ስሜታችሁን በረድ አድርጋችሁ እውነቱን ለመረዳት ጥረት አድርጉ። ጠልቃችህ ባልተረዳችሁት ነገር እነ ርዕሰ ደብር ባቦኩት ተጠልፋችሁ ከመግባት ራሳችሁን አድኑ። ይህን ብታደርጉ ራሳችሁን ወደ ሽምግልና በመለወጥ ለተለያዩ ወገኖች አስታራቂ ሽማገሌወች እንደምትሆኑ ጥርጥር የለኝም።

## 3ኛ፡- በዲሲ አካባቢና በሩቅ ላላችሁ ኦርቶዶክሳውያን ታዛቢዎች

ይህችን ጦማር ያቀረብኩላችሁ፤ በግብራቸው በመጽሐፋቸው እምነቱን የካዱ እንደ ርዕሰ ደብር አብርሃም የመሳሰሉ ደፍተሮች፤ እናንተን ቀስቅሰው በናንተ መሳሪያነት ሌላውን ወገን ለመጉዳት የሚያደርጉትን ጥረት

እንድትመለከቱ ለማሳየት እንጅ፤ ማንንም ለመደገፍና ለመጉዳት፤ ለመንቀፍና ለማዋረድ እንዳልሆነ እንድትረዱልኝ አደራ እላለሁ።

የሚያሳስበኝና፤ ሁሉም እንዲያስብበት የምመኘውም ስለ ዲሲ ቅድስት ማርያም ህንጻ ቤተ ክርስቲያን በር መስበር አይደለም። መተዳደሪያ ደንቡ መጣሱም አይደለም። ራሳቸው ሰብረው ከገቡ በኋላ ሃላፊነቱን ክደው፤ ሀለፊነቱን ለቅድስት ድንግል ማርያም ለመስጠት ማርያም ሰበረችው ማለታቸው ነው።

መተዳደሪውንም ደንብ ጥሰው; ባለ አደራውን ቦርድ አውርደው; የራሳቸውን ቦ ርድ መሰየማቸው አይደለም። ከዚያ በኋላ እያከታተሉ ያቀረቡት ውሸት እና “ማርያም በመካዷ ነው” እያሉ ማስወራታቸው ነው። የሰሯቸ ወንጀሎች በግልጽ የሚታዩ ዳኛ ፈልጎ የሚያገኛቸው ናቸው። የዳኛም ፍርድ ቢሆንም ”ካያያዝ ይቀደዳል ካነጋገር ይፈረዳል“ እንዲሉ ሊዛባ ይችላል።

እኔን የሚያስጨንቀኝ ፤ ስለነገረ መለኮት፤ ስነ ልቡና፤ ስለ ወገንና እምነት ምንም ደንታ የሌላቸው ደፍተሮች በንጹህን ካህናት አገልጋዮች ስም ራሳቸውን እየጠሩ ፤ ይህን አጸያፊ ተግባር እስክፍርድ ቤት ድረስ ይዘው መሰላፋቸው ነው። ባይን የማይታዩትን በእጅ የማይዳሰሱትን በዳኛ የማይጠገኑትን ነገረ መለኮትን፤ ስነ ልቡናንና ኢትዮጵያዊነት መናዳቸውና፤ ህዝቡንም ከዚህ ውዥንብር መክተታቸው ነው። በገንዘብ ሲጣሉ የማሸነፊያ ነገሮችንና የተከታይ ቁጥር ማብዣ በማድረግ ነገረ መለኮቱን ለናቶች በማቅረብ ማሳዘናቸው ሳያንስ፤ ለማይመለከተው ፍርድ ቤት ነገረ መለኮትን ለምን አቀረቡት ብሎ ከመጠየቅ ይልቅ፤ በጭፍን የሚከተላቸው ህዝበ ክርስቲያን መከሰቱም ኢትዮጵያውያንን ሁሉ በተለይ የገባቸውን ካህናት እጅግ የሚያሳዝን ነው።

## ምእመናን ሆይ !

በዘመናችን የተከሰቱት የሰንበት ተማሪዎች እንደሚሉት፤ የነገረ መለኮት ያተረጓጎም ስልት ወደ ህዝብ ማቅረብን፤ በብዙ ልምድ ያለፈች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ልትቀበለው ይቅርና፤ ከሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በቅርቡ የተለዩ ዘመናውያን አብያተ ክርስቲያናት እንኳ የሚቀበሉት እንዳልሆነ ላስገንዝባችሁ እወዳለሁ። ይህማ ቢሆን ሊቃውንቱ የሚመረቱባቸው ከፍተኞች ትምህርት ቤቶች መመስረት ባላስፈለጉም ነበር። ኦሬንታል ኦርቶዶክስ፤ ባዛንታይን ኦርቶዶክስ፤ ሮማን ካቶሊክና፤ ከካቶሊክ እየተገነጠሉ ከተለዩት ከነ ሉተር ጀምሮ እስከ ዚህች ቅጽበት ድረስ በመበታተን ላይ ያሉ ሁሉ ድርጅቶችን የምንመዝንበት አይኖረንም ነበር። ከዚህ ሁሉ ውዝንብር የራሳችንን መጠበቅ የምንችለው የራሳችንን ለይተን ማወቅ ስንችል ብቻ ነው።

በዚህ ዘመን እፈረሱና እየተፋለሱ ያሉት በግልጽ የሚታዩት ድንበሮችና ወሰኖች ብቻ አይደሉም። በነገረ መለኮት እውቀት ዘልቀው ያልሄዱ ሰዎች ያማያዩዋቸው እንደ ነገረ መለኮት፤ ስነ ልቡናና የመሳሰሉ ረቂቃን ጺጋዎቻችን ሁሉ እየፈራረሱ ነው። ቀደሞ ተደርጎ በማይታወቅ መልክ በሮማ ካቶሊክ፤ በኦርቶዶክስና በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ድንበር ሆነው የተቀመጡትን ነገሮች እየጎረጎሩ ወደ ህዝብ የሚደፉ ሁሉ ስውር ደባና ተልእኮ ያላቸው ሰዎች በብዛት የተከሰቱበት ዘመን እንደሆነ ተገንዘቡ። ሰባዊ ስሜቶችን አስደንጋጭና አስበርጋጊ በሆኑ ነገሮች እየቀሰቀሱ ወደ እናንተ የሚያመጡ ሰዎች በማታውቁት ነገር ውስጥ ጎትተው በመክተት ለግላቸው ጥቅም አስፈጻሚ ሊያደርጓችሁ እንደሆነ ንቁ ! እነሱ በፈጠሩት ውዥንብር ውስጥ ሳትገቡ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቁ።

1ኛ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ቀሳውስት በየዘመኑ የሞቱላት ጥንታዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ/ክርስቲያን ካቶሊካዊት ናት? እህትነቷ ለሮማ ካቶሊክ ወይስ ለኦሬንታል ?
2ኛ ቅድስት ድንግል እመቤታችንን ሮማን ካቶሊኮች፤ ኦርቶዶክሶችና ፕሮቴስታንቶች እንዴት ይገልጿታል?

3ኛ በ immculat conception በኛ አነጋገር "በግብረ መንፈስ ቅዱስ" ተጸነሰች የሚለው ትምህርት የማነው? የት ተጀመረ ?መቼ?
4ኛ መቼ ወደኛ ቤተ ክርስቲያን ገባ? ማን ከተተው?
5ኛ በዚህ ጉዳይ ኦርቶዶክሳውያን ምን አሉ?
4ኛ የቤተ ክርስቲያን ታሪክስ ምን ይላል? ለዚህ ቀጥ ያለ የማያወላውል መልስ የሌለው ካህን ተፈትኖ የወደቀ አስመስሎ የሚኖር እንጅ ኦርቶዶክስ ነው ብላችሁ አትመኑት።

ትክክለኛውን ኦርቶዶክሳዊ እምነትና ትምህርት ማወቅና መረዳት ከፈለጋችሁ "ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም በሮማ ካቶሊክ በፕሮቴስታንትና በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትያላት ግንዛቤና አክብሮት" የሚለውን ተጭነው በማንበብ የራሰወን ግንዛቤ ይውሰዱ።

ቅድስተ ቅዱሳን ልዕልት ክብት እና ንዕድ እያልን የምንላትን በስሟ የነጻ ትምህርት እድል አግኝተን የተማርንባትን እመቤታችንን እንኳ የሚፈጽሙትን ኃጢአት እሷ አደረገችው እያሉ ናቸው። እነሱ ይህንን ባያመጡ እኔም ይህን ጽፌ ለማቅረብ ባልተገደድኩ ነበር። ቅዱስ ጴጥሮስ "ለሚጠይቋችሁ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ" (1ኛ ጴ 3፡15 ) ባለው መሰረት፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አዘጋጅተውኛል። ለቀረበልኝ ሁሉ ጥያቄ ሊቃውንት አበው ባዘጋጁኝ መንገድ በምሰጠው መልስ አላፍርበትም። ማፈር የሚገባኝ የእምነትንና የእውቀትን አጉልቶ ጉድለት የሚያሳየው መወላወ ሲታይብኝ ብቻ ነው። እምነታቸውና እውቀታቸው የተወሀደላቸው ክርስቲያኖች አይወላውሉም አይጠራጠሩም። የኦርቶዶክስ መምህር ከጥርጥርና ከውልውል የራቀ ወሳኝና ቀጥ ያለ እንጅ ወላዋይና ተጥለፍላፊ ሊሆን አይገባም። መወላወልና መጠራጠር የሚያመለክተው ጉዳዩን ለይቶና አረጋግጦ አለመማርንና አለማወቅን ነው።

የመጀመሪዋ ክርስቲያናዊ ጉባዔ መሪ የነበረው ቅዱስ ያዕቆ ብ "ጥበብ የጎደለው. . . . በሁለት ሀሳብ የተያዘ በመንገዱ ሁሉ የሚወላውል ነው። አንዳች ነገር አገኛለሁ ብሎ አያስብ " (ያዕ ም 1፡ ቁ8) ያለውን ሐዋርያዊ ትውፊት በመከተል፤ መላ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት "ወንሕነሰ ንትዌከፍ ትምህርታቴሆሙ ዘመሀሩነ ወነአምን ቃላቲሆሙ ዘተፈነወ ለነ እምኔሆሙ ወእጐዛን በትምህርትነ ዘተመሀርነ ወጽኑአን ንሕነ እንበለ ተወላውሎ (ዘሱኑትዩ ሃ 110፡14) ማለትም፡- እኛስ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ የመጣውን ሊቃውንት አበው ያስተማሩንን አምነን የተቀበልነውንና ልንመሰክረውም ቃል የገባንለትን ኦርቶዶክሳዊውን እምነትና ትምህርት አጽንተን እንይዛለን" እያሉ ያስተማሩትን፤ ጥቅም በመፈለግ፤ ወይም የሚደርስብኝን ዘለፋና ስድብ በመፍራት ሳልመሰክረው እድሉ ቢያመልጠኝ ያዘጋጁኝን ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አበው መምህሮቼን መካድ እና ድክማቸውን ሁሉ ከንቱ ማድረግ ነውና እናገረዋለሁ። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ነቀፌታ የሚሰነዝሩብኝን ሰዎች እየገሰጽኩ እስካሁን ያላንዳች ማቅማማት ሄጀበታለሁ። አሁንም እሄድኩበት ነው። ወደፊትም እሄድበታለሁ።

ከንቱ ውዳሴና ከንቱ ክብር ለማግኘት ብየ፤ የከንቱ ውዳሴና ክብር ትርፍ ምንጭ ከሆኑት ብዙ ቊጥር ከሚያጅባቸው ዘመናውያን ጋራ ተሰልፌ አብሬ በማቡካት ከማገኘው ክብር ይልቅ፤ እንደነ ርዕሰ ደብር የመሳሰሉ ሰዎች የሚፈጽሙትን ስህተት እጅግ ከመጠን በላይ ቦክቶ እያየሁ "ምነው እጅግ በጣማ ቦካሳ" እያልኩ እንደ ባእድ ታዛቢ ራሴን አግልየ ሳልንቀፈውና ሳልቃወመው ማለፍ አቻልኩም። ይህችን ጦማር የምታነቡ ሁሉ ወገኖችም፤ ርእሰ ደብር አብርሃምን የመሳሰሉ ሰዎች በካሳ እያሉ ከሚያቦኩት የሸፍጥ፤ የሀሰትና የበደል ቡካት ህሊናችሁን እያጸዳችሁ በጥንታዊት ኦርቶዶክሳዊት እምነትና ትምህርት አብረን ጸንተን መቆም እንችል ዘንድ ይህችን ጦማር አቀረብኩላችሁ።
ይቀጥላል